# 8315 የኢስት ኮልፋክስ አቬኑ – የተመጣጣኝ ዋጋ ቤት አቀርቦት እና የቅድመ-መደበኛ ትምህርት

## ሳመር 2020 - በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና መልሶቻቸው

**ስለ *8315* ኢስት ኮልፋክስ ፕሮጀክት የበለጠ ሊነግሩኝ ይችላሉ?**

መርሲ ሃውሲንክ ማውንቴን ፕሌንስ (Mercy Housing Mountain Plains) ለትርፍ ያልተቋቋመ የተመጣጣኝ ዋጋ ቤት አቀርቦት ባለቤት ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ባዶ ያለውን በ 8315 ኢስት ኮልፋክስ አቬኑ እና በ 1500 ቫሌንሺያ ስትሪት መካከል የሚገኘውን ቦታ ለማልማት ከዴንቨር ከተማ ጋር አጋርነት ፈጥሯል። መርሲ ሃውሲንግ 8315 ኢስት ኮልፋክስን ጨምሮ ሁሉም ፕሮጀክቶቹ ተገቢውን መረጃ እንዲያገኙ ለማገዝ ለማኅበረሰብ ተሳትፎ ዋጋ ይሰጣል በተሳትፏቸው ላይም ይተማመናል። ከተማው ሁለቱን ቁራሽ ቦታዎች ለወደፊት የማኅበረሰብ አገልግሎት እንዲውሉ ጠብቆ ለማቆየት አልሞ በ 2017 ገዛቸው። መርሲ ሃውሲንግ ቦታውን እንዲያለማ ውድድር ባለበት የምርጫ ሂደት በከተማው እና በባለድርሻ አካላት ተመረጠ።

መርሲ ሃውሲንግ ጥራት ያላቸው እና ዋጋቸው ተመጣጣኝ የሆኑ የኪራይ ቤቶችን ለቤተሰቦች እና ለግለሰቦች ማቅረብ ላይ በማትኮር በግምት ወደ 80 የሚሆኑ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ቤቶችን ይገነባል። የአዲሱ ግንባታ የመጀመሪያው ወለል (ግራውንድ ፍሎር) በግምት 45 ለሚሆኑ ልጆች በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ እና ጥራት ያለው የቅድመ-መደበኛ ትምህርት (ECE) ማእከል ይኖረዋል።

ከማኅበረሰቡ በተሰጠው አስተያየት በመመራት እና ከቅድመ-መደበኛ ሕፃናት መዋያዎች በተገኘው መረጃ ወይም ዳታ በመረዳት መርሲ ሃውሲንግ የኢስት ኮልፋክስ መንደር ተመጣጣኝ የሆነ እና ጥራት ያለው የቅድመ-መደበኛ ሕፃናት መዋያ እና የትምህርት እድሎች የሌለው መሆኑ እና ከአቅርቦቱ ይልቅ ፍላጎቱ የበለጠበት “የልጆች እንክብካቤ በረሃ” መሆኑ ላይ አተኩሯል።

መርሲ ሃውሲንግ በሌሎች ግንባታዎቹ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ሕፃናት መዋያዎችን እና የትምህርት ማእከሎችን የመሥራት ልምዱ አለው። እንዲሁም ተመጣጣኝ የሆነ እና ጥራት ያለው የቅድመ-መደበኛ ሕፃናት መዋያ በሚኖሩበት አካባቢ መገኘቱ ለነዋሪዎቻችን እና ለሠራተኛ ቤተሰቦች ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ያውቃል።

መርሲ ሃውሲንግ በአሁኑ ጊዜ ተጨማሪ የማህበረሰብ ተሳትፎን በመፈለግ ላይ ስለሆነ ለቦታው ላለን የጋራ ርዕይ እንደመሥራታችን በልማቱ ዙሪያ አስተያየቶችን እና ግብዓቶችን ለማግኘት ከኢስት ኮልፋክስ ማኅበረሰብ፣ ነዋሪዎች እና የአካባቢው ንግድ ሰዎች አብሮ ለመሥራት ይጠብቃል።

**ልማቱ ማኅበረሰቤን እንዴት በአዎንታዊ መልኩ ይቀይረዋል?**

ልማቱ በአሁን ጊዜ ክፍት የመኪና ማቆሚያ የሆነውን ቦታ አንድ ባለአንድ ፎቅ ሕንፃ (የቀድሞ የቅዳሜ ምሽት ዳንስ ክበብ) ያለበትንና ለወንጀልና ለውንብድና ተጋላጭ ሆኖ የቆየውን የኢስት ኮልፋክስ አቬኑ እና የቫሌንሺያ ስትሪት መገናኛ ቦታን የተረጋጋና የተሻሻለ እንዲሆን ይረዳዋል። ልማቱ እንዲሁም በኢስት ኮልፋክስ መንደር ውስጥ በተመጣጣኝ ዋጋ የኪራይ ቤቶችን አማራጮችን በቋሚነት በመጨመር እና በ 8315 ኢስት ኮልፋክስ ለሚኖሩ ቤተሰቦች የቤተሰቦች አገልግሎቶችን በማቅረብ ለኢስት ኮልፋክስ መንደር የረጅም ጊዜ ለውጦችን ያመጣል። በሁለተኛ ደረጃም ማኅበረሰቡ ጥራት ያለው የሕፃናት ማቆያ እና የትምህርት እድሎችን በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኙበትን ሁኔታ ይጨምራል። የሕፃናት ማቆያ እና የትምህርት ዋጋ ተመጣጣኝነት እና በቅርበት መገኘት ለሠራተኛ ቤተሰቦች ስኬት ሁለቱ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው።

ይህን ፕሮጀክት እውን ለማድረግ እየሠሩ ስላሉ አጋሮች የበለጠ ይንገሩኝ።

መርሲ ሃውሲንግ የቅድመ መደበኛ ትምህርት (ECE) ማእከሉን እንዲያንቀሳቅስለት ከማይል ሃይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት (MHEL) ጋር አጋርነት በመፍጠሩ ኩራት ይሰማዋል። MHEL በዴንቨር ውስጥ ከ 1970 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ጥራት ያለው የሕጻናት ማዋያ እና ቅድመ መደበኛ ትምህርትን በድጎማ በሽዎች ለሚቆጠሩ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላላቸው ልጆችና ቤተሰቦች አቅራቢ ነባር እና ትልቅ ተቋም ነው።

መርሲ ሃውሲንግ ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ማእከልነት የሚውለውን የመጀመሪያው ወለልን ጨምሮ ልማቱና ግንባታውን ይቆጣጠራል። መርሲ ሃውሲንግ ዋና መቀመጫውን በዴንቨር ኮሎራዶ ያደረገ ተመጣጣኝ ዋጋ የሚኖራቸውን ቤቶችን የሚያለማ፣ የሚያድስ፣ የሚያስተዳድር እንዲሁም ለነዋሪዎች አገልግሎቶች እንዲሟሉ የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው። ባለፉት 38 ዓመታት ሜርሲ ሃውሲንግ ከ 24,000 በላይ ዋጋቸው ተመጣጣኝ የሆኑ ቤቶችን የያዙ 350 ባለብዙ ቤተሰብ እና ቅይጥ አገልግሎት ያላቸውን ልማቶች አልምቷል።

*ለ 8315 ቤቶች ብቁ እሆናለሁ?*

በልማቱ የተመጣጣኝነት ደረጃዎች ስብጥር ይኖራል። ከልማቱ ቤቶች ውስጥ በግምት 25% የሚሆኑት 4 የቤተሰብ አባላት ኖሯቸው የዓመት አማካይ ገቢያቸው $30,000 ለሆነ ገቢያቸው በጣም ዝቅተኛ ለሚባል ቤተሰቦች የሚቀመጡ ይሆናሉ። ቀሪዎቹ የልማቱ ቤቶች 4 የቤተሰብ አባላት ኖሯቸው ዓመታዊ አማካይ ገቢያቸው ከ$45,000 እስከ $60,0000 ለሆነ ቤተሰቦች የሚቀመጡ ይሆናሉ። እነዚህ ቁጥሮች ለማሳያ ያህል ብቻ የቀረቡ ናቸው። እናም መርሲ ሃውሲንግ በቦታው ለመኖር ፍላጎት ያላቸው ሁሉም ቤተሰቦች ግንባታ እንደጀመርን እንዲያመለክቱ እናበረታታለን (ለተጨማሪ ከዚህ በታች ይመልከቱ)። መርሲ ሃውሲንግ በቀጥታ ከከተማው ወይም ከሌሎች ምንጮች የሴክሽን 8 የኪራይ ድጎማ ከሚያገኙ ቤተሰቦች የመኖሪያ ቤት ማመልከቻን ሁሌም ይቀበላል።

*ለ 8315 የሕፃናት መዋያ ብቁ እሆናለሁ?*

ማይል ሃይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት (MHEL) በሕፃናት ማዋያ እና ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማእከሎቹ ከ 6 ሳምንት እስከ 5 ዓመት እድሜ ያላቸውን ልጆች ይመዘግባል። መርሲ ሃውሲንግ እና MHEL በግምት 45 የሚሆኑ ቦታዎች ለልጆች እንደሚኖሩ ይጠብቃሉ። MHEL በ “Early Head Start” እና “Head Start” የሚደገፍ ፕሮግራም ሲሆን ለኮሎራዶ የልጆች ጥበቃ እርዳታ ፕሮግራም (CCCAP) ብቁ የሆኑ ቤተሰቦችን ይቀበላል። CCCAP የገቢ መስፈርትን ለሚያሟሉ ሠራተኛ እንዲሁም ሥራ ፈላጊ ለሆኑ ወይም ስልጠና ላይ ላሉ ቤተሰቦች እና በኮሎራዶ ሠራተኛ ፕሮግራም ለተመዘገቡ እና ራሳቸውን ለመቻል የሚያደርጉትን ጥረት ለማገዝ የልጆች ጥበቃ አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች የሕፃናት ማዋያ ወጪ እርዳታን ያደርጋል። በ MHEL ለሚሰጠው የሕፃናት ማዋያ ድጎማ ብቁ የሚሆኑ ቤተሰቦች ዓመታዊ ገቢያቸው በፌደራል የድህነት መለኪያ ደረጃ ከ 100% እስከ 225% ውስጥ የሆነ ሲሆኑ ልጆቹ በማእከል እንዲመዘገቡ የየትኛው ካውንቲ ሰብዓዊ አገልግሎት እንደሚሸፍነው የሚወሰን ይሆናል።

በአጠቃላይ፣ ቤተሰብዎ የፌደራል ምግብ እርዳታ ጥቅማጥቅሞችን (ማለትም TANF፣ SNAP/EBT) ወይም የመንግስት የቤት ኪራይ ድጎማን (ማለትም፣ ..ሴክሽን 8) ወይም ሌሎች የድጎማ ገቢዎችን የሚያገኙ ከሆኑ ልጅዎ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ማእከሉ ቦታ ለማግኘት ብቁ ሊሆን/ልትሆን ይችላል/ትችላለች።

*በ 8315 የሕፃናት መዋያ ክፍያው ምን ያህል ይሆናል? ያ በዴንቨር ውስጥ ካሉ የሕፃናት ማዋያ ተቋማት ጋር እንዴት ይነጻጸራል?*

ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት (MHEL) ጥራት ያለው እና በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ የሕፃናት ማዋያ እና ቅድመ መደበኛ ትምህርት አገልግሎቶችን ገቢያቸው አነስተኛ ለሆነና የአገልግሎቶች ተደራሽነት ለሌላቸው ልጆችና ቤተሰቦች ለመስጠት የፌደራል፣ የስቴት እና የከተማ የልጆች ጥበቃ ድጎማ ፕሮግራሞች ጥምር የገንዘብ ድጋፎችን ይጠቀማል። አንድ ቤተሰብ ሊከፍለው የሚችለው በግለሰቡ ሁኔታዎች የሚወሰን እና ቤተሰቡ ለአሉት ድጎማዎች የብቁነት ሁኔታው

ላይ በመመሥረት የሚለያይ ይሆናል። ሊኖሩ የሚችሉት የገንዘብ ድጎማዎች የፌደራል "ሄድ ስታርት"ን እና የኮሎራዶ የልጆች ጥበቃ እርዳታ ፕሮግራምን (CCCAP) ያካትታሉ። እነዚህ ድጎማዎች አንድ ቤተሰብ ሊኖርበት የሚችለውን ትክክለኛ ወጭ ይቀንሳሉ። CCCAP የገንዘብ ድጎማዎችን የሚሰጠው በቤተሰቡ ገቢ እና ሥራ እንደመሥራት፣ በትምህርት ላይ መሆን ወይም ሥራ ፈላጊ መሆን ያሉ የብቁነት መስፈርቶች ላይ በመመሥረት ነው። በአጠቃላይ በ 8315 ኢስት ኮልፋክስ ለቤተሰቦች የሚሰጠው የሕፃናት ጥበቃ/ማዋያ ዋጋ በመንደሩ ውስጥ ወይም በሰፊው ማኅበረሰብ ውስጥ ድጎማ ከማይደረግላቸው አማራጮች የሚቀንስ ይሆናል። ድጎማዎች የድጋፍ ገንዘብ እንደመገኘቱ የሚወሰኑ ይሆናሉ።

*መሪሲ ሃውሲንግ ማይል ሃይ የቅድመ መደበኛ ትምህርትን እንዴት መረጠ?*

*መርሲ ሃውሲንግ ገና በ 8315 ኢስት ኮልፋክስ ልማቱን ሲጠነስስ በቦታው የሚገነባውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት (ECE) የማልማት እና የማስተዳደር ፍላጎትን ለመለካት በርካታ ጥራት ያላቸውና ተደራሽ ዋጋ ያላቸውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት (ECE) ተቋማት አንቀሳቃሾችን አነጋግሯል፣ ቃለ-መጠይቅ አድርጓል። በዚያ ሂደትም፣ ማይል ሃይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ለመርሲ ሃውሲንግ እና ልማቱ ተመራጭ ሆኖ ወጣ። መርሲ ሃውሲንግ እና ማይል ሃይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቦታውን ለኢስት ኮልፋክስ ማኅበረሰብ ወደ ተቀናጀ ልማት ለመቀየር በጋራ በመተባበራቸው ኩራት ይሰማቸዋል።*

*MHEL የሕፃናት ማዋያ ከፍተኛ ጥራትን እንዴት ይወስናል?*

*ማይል ሃይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ለ ECE አንቀሳቃሾች እና ማእከሎች ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን በሚያሰፍነው የስቴቱ ቅድመ መደበኛ ትምህርት (ECE) ይሳተፋል። የ"Colorado Shines Brightter" ግምገማ ሥርዓት 5 ማለት ከፍተኛ የሆነበት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚመሠረት ከ 1 እስከ 5 የሆነ ደረጃን ይሰጣል።* [https://www.coloradoshines.com/programs?p=Overview-of-the-ratings-process](https://www.coloradoshines.com/programs?p=Overview-of-the-ratings-process). *አሁን በሥራ ላይ ያሉት የማይል ሃይ ትምህርት ማእከሎች በኮሎራዶ ታብራለች (Colorado Shines) ፕሮግራም ግምገማ በተከታታይ 4 ወይም ከዚያ በላይ ደረጃን የሚያገኙ ናቸው። ይህም ከፍተኛ ጥራት የ ECE ትግበራዎችን እና አገልግሎት አቅርቦትን ያመለክታል። ይህ የጥራት ደረጃ ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት (MHEL) ለሠራተኞች እና ሞግዚቶች የሙያ ብቃት፣ ለቤተሰብ አጋርነት፣ ለልጆች ጤና እና ለአጠቃላይ የመማር-ማስተማሩ ከባቢ አጽንዖት ይሰጣል ማለት ነው።*

*የሕፃናት ጥበቃውን በበርካታ ቋንቋዎች ይሰጣሉ?*

*አዎ፣ ማይል ሃይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት (MHEL) ብዙ ቋንቋዎችን ከሚናገሩ ቤተሰቦች ጋር አብሮ የመሥራት ልምድ ያለው እና ብዝሃነት ላለው የሕብረተሰብ ክፍል አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ነው። ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት (MHEL) ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ ሙሉ በሙሉ አጋር እንዲሆኑ የቃል ትርጉም (ቱርጁመን) አገልግሎቶችን እና ሌሎች ተፈላጊ ግብዓቶችን ያቀርባል። በአንደኛው የማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት (MHEL) ቅድመ መደበኛ ትምህርት (ECE) ማእከል ስኬታማ የቱርጁመን አገልግሎቶችን ጨምሮ ከ 20 በላይ ቋንቋዎች ይነገራሉ።*

*ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት (MHEL) ከዚህ በፊት ከተለያዩ ባሕሎች ለመጡ ልጆች ሕፃናት ጥበቃ/ማዋያ አገልግሎት ሰጥቷል?*

*አዎ። ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት (MHEL) ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ ሙሉ በሙሉ አጋር እንዲሆኑ የቃል ትርጉም (ቱርጁመን) አገልግሎቶችን እና ሌሎች ተፈላጊ ግብዓቶችን ያቀርባል። ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት (MHEL) ለክፍል ውስጥ ብዝሃነት ዋጋ ይሰጣል፣ እናም የእያንዳንዱን ልጅ ልዩ የሆነ የባህል ውርስን የማክበር እድሉን በደስታ ይቀበላል።*

*ለሕፃናት ማዋያ/ጥበቃ የማመልከቻ ሂደቱ ምን ይመስላል? መቼ ማመልከት እችላለሁ? የተጠባባቂ ዝርዝር ይኖራል?*

*ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት* (MHEL) *ማእከሉ ከመከፈቱ በግምት* 6 *እስከ* 9 *ወራት ቀደም ብሎ የምዝገባ እቅድን ያወጣል። ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት* (MHEL) *ማእከሉ ከመከፈቱ አስቀድሞ በመንደሩ ውስጥ ብቁ ከሚሆኑ ቤተሰቦች የታሰበበት ምዝገባን ለማበረታታት በኢስት ኮልፋክስ መንደር ውስጥ በሚደረጉ የማኅበረሰብ ዝግጅቶች እና የሕዝብ መድረኮች ለመሳተፍ አቅዷል (የሕንፃ ጊዜ ሠሌዳን እዚህ በታች ይመልከቱ)። በቅድመ ልማቱ ሂደት ውስጥ ፍላጎት ያላቸው ቤተሰቦች በማንኛውም ጊዜ አድራሻቸውን ለ* MHEL *በመስጠት ስለወደፊት ምዝገባ እና በመንደሩ ውስጥ ስለሚኖሩ የመረጃ ክፍለ-ጊዜዎች ወቅታዊ መረጃ እንዲደርሳቸው ይሆናል። ማእከሉ እንደተከፈተ ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት* (MHEL) *ለሚኖሩ ክፍት ቦታዎች ጥቆማዎችን ይቀበላል፤ ተጠባባቂ ዝርዝርንም ይይዛል።*

*ለአፓርትመንቶች የማመልከቻ ሂደቱ ምን ይመስላል? መቼ ማመልከት እችላለሁ? የተጠባባቂ ዝርዝር ይኖራል?*

*መርሲ ሃውሲንግ ከሚጠበቀው የአፓርትመንቶች መከፈቻ ጊዜ* 6 *ወራት ቀደም ብሎ ማመልከቻዎችን መቀበል ይጀምራል። መርሲ ሃውሲንግ የግንባታ ሂደቱን እና የማመልከቻ ሂደቶችን ለማኅበረሰቡ በ* 8315 *ኢስት ኮልፋክስ ድር ጣቢያ* ([https://www.8315eastcolfax.org/](https://www.8315eastcolfax.org/) ) *እና ለኢስት ኮልፋክስ መንደር ማኅበር በሚደረግ የሩብ ዓመት ሪፖርት የሚያሳውቅ ይሆናል። መርሲ ሃውሲንግ በመጀመሪያ ከአፓርትመንቶቹ ይልቅ የአመልካቾቹ ቁጥር የሚበልጥ ከሆነ እጣ (ሎተሪ) የሚያወጣ ይሆናል። ሙሉ ግንባታው እንደተጠናቀቀ ለሚኖሩ ክፍት አፓርትመንቶች መርሲ ሃውሲንግ የተጠባባቂዎች ዝርዝርን ይይዛል።*

*የሕንፃው ግንባታ መቼ ይጠናቀቃል?*

*የሕንፃው ግንባታ መጠናቀቅ ከከተማው፣ ከስቴቱ እና ከፌደራል ምንጮች በሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ ላይ የሚወሰን ይሆናል። ቀሪው የ* 2020 *ጊዜ ለመኖሪያ አፓርትመንቶቹ እና ለቅድመ-መደበኛ የሚፈለገውን ገንዘብን ለማግኛ ጥረት የሚውል ይሆናል። መርሲ ሃውሲንግ የገንዘብ ድጋፉን ካገኘ በቦታው ላይ የግንባታ ልማቱን በ* 2021 *ሳመር መገባደጃ የሚጀምር እና በ* 16 *ወራት ጊዜ ሰሌዳ ውስጥ የሚያስረክብ ይሆናል። ከዚያም የመኖሪያ አፓርትመንቶቹ እና የ* ECE *ማእከሉ በ* 2022 *መገባደጃ ተጠናቅቀው ይከፈታሉ።*

*የኢስት ኮልፋክስ ማኅበረሰብ ለእነዚህ አገልግሎቶች ቅድሚያ የሚኖረው መሆኑን መርሲ ሃውሲንግ እንዴት ለማረጋገጥ ይችላል?*

*መርሲ ሃውሲንክ ማውንቴን ፕሌንስ* (MHMP) *እና ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት* (MHEL) *የተወሰኑ የ* ECE *ቦታዎችን ገቢያቸው እጅግ በጣም ዝቅተኛ ለሆኑ ቤተሰቦች ቅድሚያ እንዲሰጡ ትኩረታቸውን ያደርጋሉ። እንዲሁም በግምት ከሦስት አራተኛ እስከ ግማሽ የሚሆኑት ቦታዎች ለመላው ማኅበረሰብ ልጆች እንደሚደረጉ እንገምታለን። በፌደራል ፍትሐዊ የቤት አቅርቦት ደንብ መሠረት መርሲ ሃውሲንግ የመኖሪያ ቤቶቹን በአሁኑ ጊዜ በመንደሩ ውስጥ ለሚኖሩ ወይም ከዘመዶች ጋር ተዳብለው ለሚኖሩ ቤተሰቦች እና ግለሰቦች ቅድሚያ የሚሰጥ ይሆናል።*

*እንደዚሁም፣ ማይል ሃይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት* (MHEL) *በ* “Head start” *እና* “Early Head Start” *ፕሮግራሞች የሚደጎሙ ቦታዎችን ለልጆች ለመስጠት የፌደራል የምርጫ መስፈርቶችን እንዲጠቀም ይገደዳል።* MHEL *መስፈርቱን ለሚያሟሉ የኢስት ኮልፋክስ ቤተሰቦች ምዝገባ ወይም መረጣ ለማድረግ በአካባቢው የማኅበረሰቡ ዝግጅቶች፣ ት/ቤቶች እና እምነት በሚጣልባቸው የመንደሩ ባለድርሻ አካላት አማካኝነት የቤተሰቦችን ተሳትፎ የሚያካትት ጥረትን ያካሂዳል።*